# አይበጅም ጋንግሪን

እንኳንስ ለሃገር ፣ እዚያው ለጎጣቸው
ጠመኔ እማይገዛ ፣ ቢሰላ ዋጋቸው
ይላስ የሚቀመስ ፣ አንዳች የሌላቸው
የሰረቁት ቤሳ ፣ የሚያኖር መስኋቸው
እንቡር እንቡር ካሉ ፣ ጥጋብ ከነፋቸው
ቁልቋሉን ይጋግሩት ፣ ጤፍ ከሆነላቸው ።

እግዜሩም ሲጣላ ፣ በቅድሚያ ደግሶ
ጳጳሱ ያሳዩን ፣ ጺዮን ማርያም ነግሶ
ሰማይ እንዳልወጡ ፣ ከምድር መልሶ
ከነ ግብራበሩ ፣ ቡቱቱውን ለብሶ
አልማር ያለውን ፣ አፈር ትቢያ አልብሶ
ውስኪ እንዳልተራጨ ፣ ቁልቋሉን አጉርሶ
እንሰማለን ገና ፣ ጫጫታና ለቅሶ
የጠገቡ ለታ ፣ ችጋሩ መቼ ታውሶ !!

የትላንቱ ቁምጣ ፣ ቡቱቱ ዲሪቶ
ዛሬ በገበርዲን ፣ ሲያየው ተተክቶ
ያሳለፋት ማከክ ፣ ትላንትን እረስቶ
ትዕቢት ከወጠረው ፣ ካበዛ ቀረርቶ
እንኳን ተመኝቶ ፣ ልቡን አሸፍቶ
እንጦሮጦስ ይውረድ ፣ ባፍጢሙ ተደፍቶ
ማባረር ነው ጭራሽ ፣ ካስፈለገም ገፍቶ ።

ወረቱ እንዳማረ ፣ እንደ እህል ነጋዴ
ተለይቶልናል ፣ ገለባው ከስንዴ
መንገዱን ያበጃል ፣ ፈጣሪም አንዳንዴ
መሸኘት ነው መላው ፣ እንዲያውም በዘዴ
ትርፉ በሽታ ነው ፣ ቁርኝት ከውርዴ ።

እረፍት የነሳህን ፣ የመጣን አግጥጦ
ሁኔታውን አይቶ ፣ መርምሮና አድምጦ
ጤና ያልሰጠህን ፣ አስተውሎ መርጦ
በሽታው ስር ሳይሰድ ፣ ሳይበላህ አላምጦ
ማረፉ ይበጃል ፣ ጋንግሪኑን ቆርጦ ።

ሟርተኛ ፖራሳይት ፣ መቃብር ቆፋሪን
የያዛቸው ደዌ ፣ እንዳይበክል ቀሪን
የዘር የጥላቻ ፣ ዘዋሪ ሾፋሪን
የሳር ውስጥ እባቦች ፣ ፅንፈኛ መሰሪን
ቆርጦ መገላገል ፣ አይበጅም ጋንግሪን ።

ታዛቢው

December 10, 2018